በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር ፌ/ጠ/ዐ/ሕግ/ፀ/ፀ/ተ
Ref.No
ቀን 22-10 2009
Date

በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

ልደታ ምድብ ወንጀል ችሎት

<u>አዲስ አበባ</u>

የፌ/ጠ/ዐ/ህ/መ/ቁ 280/09

የፌ/ፓ/ወ/መ/ቁ 494/09

ከሣሽ ------------- የፌ/ጠ/ዐ/ህግ

ተከሣሾች ---------1ኛ ኦሊያድ በቀለ ደብሬ (ቅጽል ስሙ ቶኪቻ ሙርቴሳ፣ታከለ)

ዕድሜ 26 ሥራ አርቲስት

አድ/ አ/አ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ቀበሌ 12

2ኛ ሞይቡል ምስጋኑ ወርቅነህ ቅጽል ስም፣ኖሴቡታ፣ሙላቱ

ምስጋኑ፣ሞይቡል ብሉ ቀዌ) ዕድሜ 30 ሥራ

አድ/ አ/አ ጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ሚሊኒክ የም ሥፈር፣

3ኛ ቀነኒ ታምሩ ጀፈር/ቅጽል ስም አስሊ ኦሮሞ/ ዕድሜ 29

የት/ደረጃ የቀለም ትምህርት 3 ዓመት የተማረች

አድ/ኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ ቀበሌ ከታ

4ኛ ሊቹ ገመቹ ለታ በቅጽል ስሙ ሀሪሮ ጆርጎ/ጃፈር አሊ ኤሌም/እድሜ 44

አመት አድራሻ ኦሮሚያ ክልል ምስ/ሸዋ ቢሾፍቱ ቀበሌ 14

5ኛ ባይሉ ነጮ ታደሰ በቅጽል ስሙ ኢርቡ ሰባ /በሃይሉ ነጮ/ እድሜ 26

አመት አድራሻ ኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከታ

6ኛ ሴና ሰለሞን አምበቻ እድሜ 25 አመት አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ

ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 10

7ኛ ኤሊያስ ክፍሉ በቀለ በቅጽል ስሙ ዳንኤል/ዳኒ እድሜ 27 አመት

አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 8



Scanned by CamScanner

ቁጥር___________
Ref.No
ቀን___________
Date

## 1ኛ ክስ

## በ1ኛ እና በ4ኛ ተከሣሾች ላይ ብቻ

## ወንጀል

በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀናለ፣ 38/1/ እና የፀረ-ሽብርተኛነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ፡

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን፣ በመላ ሀሳባቸው እና አድራጎታቸው በወንጀሉ ድርጊት እና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን፣ ኦሮሚያን ክልል ከኢትዮጵያ ፌዴራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባልነት በሀይል ለመገንጠል፣ የሀገሪቱ ህዝቦች አንድነት ለመሸርሸር ዓላማ ይዞ እና አላማውን ለማስፈፀም እና ህ/ሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት፣ በመንግስት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር፣ የሃገሪቱን መሰረታዊ ፓለቲካዊ፣ ህገመንግስታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይም ለማፈራረስ ከሚንቀሳቀሰው እና ኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦ.ነ.ግ) ብሎ እራሱ የሚጠራውና፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኝነት የተሰየመው ሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ አባል በመሆን፣በውጭ ሀገር ከሚገኙ የሽብር ድርጅት አመራሮችና አባሎች ጋር በስልክ፣ በኢ.ሜይል፣በፌስቡክ ግንኙነት በማድረግ፣ ተልዕኮ በመቀበል የኦነግ ሰገሌ ቂሮ (የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ወጣቶች ድምጽ) በሚል በመደራጀት፣ ህዝቡ ለአመጽ፣የሚያነሳሳ ዘፈኖችን በማዘፈንና በመዝፈን፣በጽሁፍ ዜና በማዘጋጀት ሪከርድ በማድረግ በውጭ ሀገር ላሉት የኦነግ አመራሮች የተዘጋጀውን ዜና በኢ.ሜይል በመላክ፣ በውጭ ሀገር ባሉት የኦነግ አመራሮች አማካኝነት ለተለያዩ ማህበራዊ ድረ ገጽ እንዲሰራጩ በማድረግ፣ ህዝቡ ወደ አመጽና ብጥብጥ ውስጥ ገብተው የሽብር ወንጀል እንዲፈጽምና በማነሳሳት የሰው ህይወት እንዲጠፋ፣ በመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆነ ተቋማት፣ እንዲሁም በግለሰብ ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ ሲያነሳሱ የቆዩ ሲሆን በተለይም፡-

1ኛ ተከሳሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በመጋቢት ወር 2007 ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ በአዲስ አበባ በጉለሌ ክ/ከተማ አካባቢ በሚገኙ አዲሱ ከረዩ እስቱድዩ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ


ፋክስ
FAX 0115-51-77-75
ፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1370
ስልክ
Tel. 0115-51-50-99
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa - Ethiop

Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

ግርማ ጥሩነህ (በቅጽል ስሙ አብዲ) በተባለ የሽብር ቡድኑ አባል አማካኝነት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ሰገሌ ቂሮ /የኦነግ ወጣቶች ድምጽ) በሚባል በሽብር ቡድኑ ውስጥ ዜና አንባብ ሆነህ፣ በየወሩ 2000 (ሁለት ሺህ) ብር እየተከፈለህ፣የኦነግ አባል በመሆን ትሰራለህ ወይ? በማለት ያቀረበለትን ጥያቄ በመቀበል እና በሀሳቡ በመስማማት አባል በመሆኑ፣

1ኛ ተከሣሽ ቀኑ እና ወሩ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በ2007 ዓ/ም ግርማ ጥሩነህ በተባለ የኦነግ አባል አማካኝነት በውጭ ሀገር ከሚገኘው የኦነግ አመራር ጋሹ ለሚሳ /ጫቶ/ ከተባለው ጋር በስልክ አስተዋውቆት የኦነግ አመራሩም ተከሳሽ አዲስ አባል እንዲመለምል እና እንዲያደራጅ ተልዕኮ ሰጥቶት ተልዕኮውን በመቀበል፣ ቀኑ እና ወሩ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀ በ2008 ዓ/ም ላይ ባይሉ ሲጮ፣ ኤቢሳ ዋቅጋሪ፣ ሴሲሴ መኮንን የተባሉትን በቡራዩ ከተማ እና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለኦነግ ሰገሌ ቂሮ (ለኦነግ የወጣቶች ድምጽ) በሚል በተቋቋመው የሽብር ቡድን ለዜና አንባብነት የመለመላቸው በመሆኑ፣

1ኛ ተከሳሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀ በመጋቢት ወር በ2007 ዓ/ም ላይ ኢፋ ገመቹ (2ኛ ተከሳሽ) በተባለ የሽብር ቡዱን አባል ጋር በመሆን፣ አመጽ፣ብጥብጥ እና ረብሻ እንዲቀሰቀስ እና የሽብር ወንጀል እንዲፈፀም ለማነሳሳት በማሰብ፣ በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች፣ እንዲሁም በተለያዩ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ፀጥታ አካሎች ያለምንም ምክንያት ህዝቡንና ተማሪዎችን እየደበደቡ እና እያሰቃዩ ናቸው በማለት የኦነግ ሰገሌ ቂሮ/የኦነግ የወጣቶች ድምጽ/ በሚል በተቋቋመው የሽብር ቡድን በጽሁፍ ዜና በማዘጋጀት በድምጽ ሪከርድ በማድረግ ውጭ ሀገር ላለው የኦነግ አመራር ለሆነው ጋሹ ለሚሳ/ጫቶ/ ለተባለ በኢ..ሜይል እና በፌስቡክ በመላክ በእሱ አማካኝነት ለተለያዩ ማህበራዊ ድረ-ገጽ እንዲያሰራጭ እያደረገ የቆዩ በመሆኑ፣

1ኛ ተከሣሽ በ0960235635፣0920687993 በመጠቀም በሀገር ውስጥ እና በውጭ ከሚገኙ የኦነግ አባሎች እና አመራሮች ጋር ሲለዋወጣቸው የነበሩ መረጃዎች እና መልዕክቶች በዝርዝር ሲታይ በ25/1/2009 ዓ/ም በአዲስ አበባ እና በአሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን በቡራዩ ከተማና አካባቢው ያለውን ሁኔታ ምን እንደሚመስልና በቂሮ ድምጽ በሚል በኦሮምኛ ቋንቋ የሚያስተላልፉትን አማረኛ ቋንቋ የሚችል ሰው ካገኙህ በኦሮምኛ የተዘጋጀው ወደ አማረኛ ቋንቋ አስተርጉሞ እንዲልክለት በውጭ ሀገር የሚገኙ ስሙ ያልተጠቀሰ አንድ የኦነግ


ፋክስ FAX 0115-51-77-75 | ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1370 | ስልክ Tel. 0115-51-50-99 | አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethio

Scanned by CamScanner

አመራር ለ1ኛ ተከሳሽ ትዕዛዝ የሰጠው መሆኑ፣ በ27/1/2009 ዓ/ም አዲስ አበባ የሚገኘው እና የኦነግ ሰገሌ ቄሮ /የኦነግ የወጣቶች ድምጽ/ አስተባባሪ የሆነው 1ኛ ተከሳሽ በስልክ ውጭ ሀገር ላለው ስሙ ላልተጠቀሰ አንድ ለኦነግ አመራር ስልክ ደውሎለት በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን በቡራዩ አካባቢ የተጀመረው አመጽ እንደቀጠለ መሆኑና በተቀሰቀሰው አመጽ ምክንያት አንድ ሰው በፀጥታ ኃይሎች እንደተገደለ በመጠቆም፣ ቀደም ሲል ወደ አሜሪካ በመተርጎም የሚያቀርብላቸው የነበረው ሊሉ የተባለ ያባቱ ስም ያልታወቀ የኦነግ ሰገሌ ቄሮ (የኦነግ የወጣቶች ድምጽ) አባል የነበረው ከታሰረ በኃላ ደህና ሰው ማግኘት እንዳልቻሉ በመግለጽ በውጭ ሀገር የሚገኘው የኦነግ አመራር እራሱ የሚያውቃቸው አባላት ካሉ እንዲያገናኛቸው የገለጸለት መሆኑ፣ በ14/2/2009 ዓ/ም በውጭ ሀገር የሚገኙ የኦነግ አመራር በሀገር ውስጥ ያሉትን የኦነግ አባላት ስም ዝርዝር መጠየቃቸውን በመጥቀስ በእጇ ላይ የደረሰ ካለ እንድትልክላቸው 1ኛ ተከሳሽ አዲስ አበባ ለነበረችው ሴሲሴ የተባለች ያባቱ ስም ያልተጠቀሰ የኦነግ የወጣቶችድምጽ /የኦነግ ሰገሌ ቄሮ / አባል የሆነችዋን ጠይቋት፣ ሴሲሴም በበኩሏ ለጊዜው የአባታቸው ስም ያልታወቀ የሶስት አባላት ስም ዝርዝር የደረሳት መሆኑ ገልፃለታለች፣ በተጨማሪም ቢሾፍቱ መከላከያ ተቋም ውስጥ የሚሰራ አንድ ሰው የታሰሩትን እና ስራ ላይ የነበሩትን ሰዎች ሙሉ ስም በ21/2/2009 ዓ/ም እሰጥሻለሁ እንዳላትና በሌላ በኩል በቢሾፍቱ ኢንፎርሜሽን እየሰበሰቡ የሚሰጧትን ከተማሪዎች፣ ከዋቄ ፊታ እና ከመንግስት ሰራተኞች አንዳንድ ሰው አግኝታቸው ተልዕኮ የሰጠቻቸው መሆኑን ለ1ኛ ተከሳሽ ገልፃለታለች፡፡ ግርማ ጥሩነህ (ቦምባ) ከተባለ ጋር በኦነግ ቄሮ (የኦነግ ወጣቶች) ይሰራ የነበረ ዳዊት ታደሰ የተባለ አባላቸው ይኖርበት ከነበረበት ቤት አስወጥተውት ችግር ውስጥ ያለ መሆኑና ልጁ ለኦሮሞ ህዝብ የሰራ እና እየሰሩ ያለ ስለሆነ ድርጅቱ የተወሰነ ገንዘብ ድጋፍ ቢያደርግለት እና በሌላ በኩል ለማውጣት ያዘጋጀው ዘፈን ቀረፃው ሱሉልታ አካባቢ እንደሚካሄድና የዘፈኑም ይዘት ሲታይ መፎክሮች ያሉበትና ለትግል ወጣቶችን የሚያነሳሳ ስለሆነ ዘፈኑን በአሁን ጊዜ ገበያ ላይ ቢያውለው ለደህንነቱ ጥሩ ስለማይሆን ሁኔታዎቹ ከተረጋጉ በኃላ እንደሚለቅ በመግለጽ አስፈላጊ ከሆነ ኦዲዮውን እንደሚልክለት አዲስ አበባ የነበረው በሀገር ውስጥ የኦነግ ቄሮ /የኦነግ ወጣቶች/ አስተባባሪ የሆነው 1ኛ ተከሳሽ ውጭ ሀገር ለነበረው ጋሹ /ጫቶ/ ለተባለ የኦነግ አመራር ለሆነው በ20/2/2009 ዓ/ም የገለጸለት



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

ሲሆን፣ በውጭ ሀገር የሚገኙ የኦነግ አመራር የሆነው ጋሹ /ጫቶ/ የተባለ በበኩሉ ኤባዋቃዩ የተባለ አርቲስትም በተመሳሳይ መልኩ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ጥያቄ እንዳቀረበላቸው በመጠቆም 1ኛ ተከሳሽ የሆነው አልያድ በቀለ የኦነግ ቄሮ (የኦነግ ወጣቶች) የሀገር ውስጥ አስተባባሪ የሚያምንባቸው ሰዎች ካሉ ድጋፍ ለማድረግ ወደኃላ እንደማይሉና ዳዊት ለተባለው አንድ ሺህ (1000) የአሜሪካን ዶላር ተሾመ የተባለ በውጭ ሀገር የሚገኙ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አመራር የሆነው ገንዘቡን እንዲልክለት በኢ.ሜ.ይ.ል እንደገለጸለትና ለመልቀቅ ያዘጋጀውን ዘፈን እንዲልክለት እና ቀነኒ የተባለች በመንግስት ቁጥጥር ስር ስለመዋሏ ኢንፎርሜሽን እንደደረሳቸው በመግለጽ የት እንደታሰረች አጣርቶ መረጃ እንዲሰጠው 1ኛ ተከሳሽን ያዘዘው መሆኑ፣ ከተለያዩ

ከመንግስት ተቋም ውስጥ 30 አባላት ስም ዝርዝር የተላኩትን ጊዜ ወስደው ቁጭ ብለው ከተነጋገሩበት በኃላ በውጭ ሀገር ለሚገኙት ለኦነግ አመራሮች እንደሚልኩላቸውና ለጋሹ (ጫቶ) ለተባለ የኦነግ አመራር በኢሜይል የሚልክለትን መልዕክት ጋሹ (ጫቶ) በስሩ ስለተወጠረ እራሱ ሳይሆን በሌላ ሰው ኦማካኝነት መልስ እየተሰበሰው መሆኑን እንደተረዳና፣ ለኦነግ አመራሮች በእስር ላይ ስለሚገኙ የአስራ አንድ አባላት ስም ዝርዝር ጉዳይ ተሾመ ለተባለ በውጭ ሀገር ለሚገኙ የኦነግ አመራር እንስቶለት ተሾመም በበኩሉ ከጋሹ (ጫቶ) ከተባለ የኦነግ አመራር ጋር ተነጋግረን መልስ እንሰጠሃለን ብሎ እንደገልፀለት አዲስ አበባ የነበረው የሀገር ውስጥ የኦነግ ቄሮ አስተባባሪ የሆነው 1ኛ ተከሳሽ በ24/2/2009 ዓ/ም አዲስ አበባ ለነበረች ሌሊሴ (3ኛ ተከሳሽ) ለተባለች የኦነግ ቄሮ (የኦነግ ወጣት) አባል ስሆንችሁ ገልጸላት፣ ሌሊሴም በበኩሏ የ30 አባላትን ስም ዝርዝር ለላከላት ሌላ አባላቸው አምስት መቶ (500) ብር በባንክ እንደላከችለት በመጠቆምና ጋሹ የተባለ የኦነግ አመራር በስራ የተወጠረ መሆኑን ፍሰሃ የተባለው በውጭ ሀገር የሚገኘው የኦነግ አባል እንደገለፀላት በመጠቆም፣ በሁሉም ጉዳዮች ዙሪያ በአካል ተገናኝተው መነጋገር እንዳለባቸው ለ1ኛ ተከሳሽ የገለፀችለት በመሆኑ፣ በአሜሪካን ሲያትል ከተማ ያዘጋጁት ፕሮግራም ለማዘጋጀት ያነሳሳቸው ነገር ምን እንደሆነ፣ በቅርቡ በሀገር ውስጥ የሚገኙት ቄሮ ቢሊሰማ (ወጣቶች ለነፃነት) በአሮሚያ ክልል የጀመረው የአመጽ እንቅስቃሴ ውጭ ሀገር የሚገኘው የኦሮሞ ዲያስፓራ (ዲያስፎራው) እንዴት እንደሚያዩት፣ ቄሮ ቢሊሱማ (ወጣቶች ለነፃነት) እያደረገ ያለው የአመጽ እንቅስቃሴ ከዚህ



Scanned by CamScanner

በተመሳሳይ ቀን ቢያአሮሞ የተባለውም እሺ እደውልልሃለሁ እኔም ሩንዴሳ እባላለሁ ሲል የገለጸለት መሆኑ፣

1ኛ ተከሳሽ በ29/6/2008 ዓ/ም ታቦሬ ወጋ ለተባለ በውጭ ሀገር ለሚገኙ የኦነግ አመራር እኔ እንደሚታወቀው የቄሮ ድምጽ /እኔ የወጣት ድምጽ/የተባለው አካል እየመራሁ ነው ለማለት ይከብደኛል ጓድ ሐሪሮ ስራ እያበላሸ ነው እኔ የራሴ የሆነ የትግል ታሪክ አለኝ ስራዬንም በሚስጥር ነው የሚያከናውነው ሌላው" በባርነት ፍፃሜ አመጽ" ላይ ለተጎዱ አባላት ድጋፍ የሚውል በኬሮን ደረጃ (አያኔ ካቶ) በኩል የላካችሁትን ገንዘብ አዳማ ከተማ ሀይለማሪያም ማሞ ሆስፒታል ውስጥ በመታከም ላይ ለምትገኘው ደራርቱ መሀመድ ለተባለች ሰጥቻለሁ፣ ሴት አባሎቻችን መዋቅራቸው እየሰሩ ነው ድጋፍ እንዲደረግ ለሌሎች ጓዶችም እንድታስረዱልን መልዕክቴን አስተላልፋለሁ በማለት ለታበሬ ወጋ ሲገልጽለት ታቦሬ ወጋ የተባለውም ደግሞ ሀሳብህን ተረድቻለሁ ገንዘብ በአንተው ስም ይላክለሃል በማለት ለ1ኛ ተከሳሽ በ6/7/2008 ዓ/ም ገልጾለታል።

1ኛ ተከሳሽ በ14/7/2008 ዓ/ም ለታቦሬ ወጋ በላከው መልዕክት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሰሩ ተማሪዎች ሪፓርት ልኬልህ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ገልጬልሃለሁ፣ የታሰሩ ተማሪዎች እንዲለቀቁ በመማር ላይ ያሉት ሰልፍ ለመውጣት ለማክሰኞ ተዘጋጅተው ሳይሳካ ስለቀረ ለሐሙስ በ1/8/2008 ዓ/ም በሶስት ሰዓት ላይ በእንግሊዝ ኤምባሲ ተቃውሞ ለማሰማት ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑንና ጃል ሀሪሮ የተባለ አባላችን ከፈረንጆቹ ጋር ግንኙነት ስላለው ሁኔታውን እንዲከታተል መልዕክት እንዲያስተላልፍላቸው ነግሬዋለሁ በማለት የገለጸለት በመሆኑ፣

1ኛ ተከሳሽ ከ5/12/2008 ዓ/ም እስከ 29/3/2009 ዓ/ም ድረስ ውጭ ሀገር ከሚገኙ የኦነግ አመራሮችና አባሎች ከሆኑት 1ኛ ኩመራ ዋቅጅራ፣ ከተባለ 999.99፣2ኛ ከምስጋኑ ዲስካታ ከተባለ 800፣3ኛ ዋቅጅራ ከተባለ የአባቱ ስም ካልተጠቀሰ 800 የአሜሪካ ዶላር በ1ኛ ተከሳሽና በተለያዩ የሽብር ቡድኑ አባሎች ስም ከኦሮሚያ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ከኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ አ.ማ ለስራ ማስፈፀሚያ በሚል ሲላክለት የነበረ በመሆኑ፣

1ኛ ተከሳሽ በ30/8/2008 ዓ/ም ለተለያዩ ስራዎች ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ የሚቀበል [illegible] የበል[illegible] ሰው ሙሉ አድራሻ አዘጋጁ ብለህ በጠየከን መሰረት መርጋ ሽመልስ አበራ የተ[illegible]



Scanned by CamScanner

ቁጥሩም+ 25194 5309133 ነው በማለት በውጭ ሀገር ለሚገኙ የኦነግ አመራር ለሆነው ለታቦሬ ወጋም በተመሳሳይ ቀን መልዕክትህ ደርሶኛል በርቱ ስራውን አጠናክራችሁ ቀጥሉ ከመስመርም አትጥፉ ያዘጋጀውን ሪፓርት በፍጥነት ላክልኝ ሲል የገለጸለት በመሆኑ፣

1ኛ ተከሣሽ በ14/9/2008 ዓ/ም ለስራ ማስፈፀሚያ የተላከው ገንዘብ እስካሁን አልደረሰንም በማለት ላቀረበው ጥያቄ ታቦሬ ወጋ የተባለ በውጭ ሀገር የሚገኙ የኦነግ አመራር ለቀረበለት ጥያቄ በተመሳሳይ ቀን የመለሰው በጌትነት ጀቤካ ስም የተላከ የገንዘብ መጠኑ ስምንት መቶ (800) ዶላር፣ በከቢር አባጉምቡል ስም የተላከ የገንዘብ መጠኑ ዘጠኝ መቶ (900) ዶላር ነው ከሁለቱ ሰዎች ስም አንድ ሺህ ሰባት መቶ (1700) ዶላር የተላከልህ ስለሆነ ገንዘቡን እንደተቀበልክ እንድታሳውቁኝ በማለት የገለጸለት በመሆኑ፣

1ኛ ተከሣሽ ቀኑ እና ወሩ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት ከ2008 ዓ/ም የኦነግ እስከ በቁጥጥር ስር ከዋለበት 2009 ዓ/ም የኦነግ ሰገሌ ቄሮ (ኦነግ ወጣቶች ድምጽ)አባል በመሆን፣ በመጨረሻ ላይም የኦነግ ሰገሌ ቄሮ/ኦነግ ወጣቶች ድምጽ) ዜና አዘጋጆች በሚል በተቋቋመው የሽብር ቡድን ኃላፊ በመሆን፣ በውጭ ሀገር ከሚገኙ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አመራሮች እና አባሎች ጋር በሰነድ ማስረጃነት በገለጽነው አግባብ በፌስቡክ እና በኢሜይል በመጠቀም ህዝቡን ለአመጽ፣ ለብጥብጥ ረብሻ እንዲነሳሳና የሽብር ድርጊት እንዲፈጸም የሀሰት መረጃዎችን በዜና መልክ በማዘጋጀት ሲፃፃፍ የነበረው፣ በኦሮሞ ነፃነት ትግል የተገኘው የእሬቻ በዓል፣ ከኦሮሞ ቄሮ ቢሊሱማ (ከኦሮሞ ወጣቶች ለነፃነት) የተሰጠ መግለጫ፣ የወያኔ ስርዓት በህዝባችን ላይ የሚያደርሰው ጫና፣ ወያኔ የእሬቻ በዓልን ወደ የጨለንቆና አኖሌ ጦርነት በመቀየሩ፣ ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ከኦነግ) ስራ አስፈፀሚ ኮሚራ የተሰጠ ጠቅላላ መግለጫ፣ የኦሮሞ ነፃነት ታጋይ መሪዎች፣አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ለኦነግ ካድሬዎች በሙሉ፣ የወያኔ መንግስት እና ተላላኪዎችን አስመልክቶ በሚል፣ በወያኔ መንግስት እና ተላላኪዎን አስመልክቶ በሚል፣ በወያኔ መንግስት ጦር ውስጥ የሚገኙ እና በሁሉም ደረጃ ያሉ የመንግስት ሰራተኞች ለሆኑ የኦሮሞ ልጆች፣ በተለያዩ የመንግስት መዋቅር ውጪ ላሉት ህዝቦችና ወጣቶች፣ውጭ ሀገር የሚኖር የኦሮሞ ማህበረሰብ አስመልክቶ በሚል፣ብሄራዊ የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነት እና ለዲሞክራሲ፣የወያኔ መንግስት ህፃናትን፣ሴቶችን፣እርጉዝ ሴቶችን፣አረጋዊያንን ብዛታቸው 443,238 የሚሆኑትን በኢትዮጵያ


ፋክስ FAX 0115-51-77-75
ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1370
ስልክ Tel. 0115-51-50-99
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethio

Scanned by CamScanner

ጦር ካምፓዎች፣ በዴዴሳ፣ በታጠቅ፣ በብላቴ፣ በጦላይ፣ በሁርሶ፣ በሆለታ፣ በሰንቀሴ እና በጅግጅጋ እስር ቤቶች አጉሮ በኤሌክትሪክ እያቃጠለ፣እየገረፈ እያሰቃዬና እየገደለ በሚል፣ በኦሮሞ ልጆች ላይ የሚፈፀመው ግድያ ኤፍ ኤክስጂን /Fiinciila xuumura gabrumaa) "የባርነት ፍፃሜ አመጽ" ወደኃላ አይመለስም የቄሮ ቢሊሱማ/የወጣቶች ለነፃነት) አሮሞ መግለጫ በሚል፣ የኦሮሞ ፀረ ባሪነት እንቅስቃሴ ወቅታዊ የኦሮሞ ፀረ-ባሪነት ትግል ከህዳር 2007-ነሐሴ 2008 ዓ/ም በሚል፣ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኦሮሞዎች፣ በሀገር ውስጥ የሚኖር ኦሮሞ ማህበረሰብ በሀገር ውስጥ የሚያደርገው እንቀስቃሴ ለመረዳት ብዙ እድሎች አሉ በሚል፣ የኦሮሞ ለነፃነት የቄሮ ኦሮምን (የኦሮሞ ወጣቶችን) ተቃውሞ የሚደግፍ እና ጥያቄውን ሰምተው አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት የሁሉም ኦሮሞ ግዴታ እንደሆነ በሚል፣ ድል ለኦሮሞ ህዝብ ገዳው የነፃነት ነው፣ ቄሮ ቢሲሱማ /ወጣቶች ለነፃነት/ ኦሮሞ ፣(ጥራዝ 11)፣የኦሮሞ ህዝብ የባርነት ተቃውሞ እንቅስቃሴ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ከሀገር ውስጥ የኦሮሞ ነፃነት እና ቄሮ/ወጣቶች/ በሚል (ጥራዝ 12)፣ ታቦሬ ወጋ፣ ግንቦት 23፤ ዲና ዲግ/ጠላትን በትን/ ግንቦት 23 ለገዳ፣ ታቦሬ ወጋ፣የፀረ ባሪነት ትግል በአዲስ መልክ በወለጋ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ፈንድቷል በሚል፣ታቦሬ ወጋ ግንቦት 23፣ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ወለጋ ዞን ኪረሙ ወረዳ ሌሊስቱ ሀሮ ት/ቤት ውስጥ ትላንት ግንቦት 22 የፀረ-ባሪነት ትግል እንቅስቃሴ ተደርጎ መንግስትን ሲያሰጨንቅ እንደዋለ በሚል፣ታቦሬ ወጋ ግንቦት 19 በመላው ኦሮሚያ የጸረ-ባሪነት ትግል 5 ዙር ፊንፊኔ ከተማን ጨምሮ በኦሮሚያ ዞኖች በአጠቃላይ እንቅስቃሴው ተጠናክሮ ቀጥሏል በሚል፣ ግንቦት 17 ቀን የቄሮ ዞን ሪፓርት /የወጣቶች ዞን ሪፓርት/፣ ታቦሬ ወጋ ግንቦት 18 ሀረሚያ ዩኒቨርስቲ ቄሮ /ወጣቶች/ ዛሬ ያስተላፈ ሪፓርት፣ ታቦሬ ወጋ በምዕራብ ሀረርጌ አስቦት አካባቢ የፀረ-ባሪነት ትግል ቀጥሎ ዋለ በሚል፣ከነጆ ከተማ ወደ ቤንሻንጉል ክልል የሚወስደው መንገድ በቄሮ/በወጣቶች/ ተዘጋ በሚል፣ነፃነት ደርሷል ኦሮሞ ለምን ትቀመጣለህ ተነስ ነፃነትህን ተቀዳጂ ትግላችን መቼም አይቆምም በሚል፣ዲና ዲግ (ጠላትን በትን) ግንቦት 14 ለታቦሬ ሰላምታ ይቅደም የላካችሁት ገንዘብ ደርሶናል የቄሮ ድምጽ /የወጣቶች ድምጽ) በአንድ ሶፍትዌር እስከ አሁን ስራውን እየሰራ ነው በሚል፣ ታቦሬ ወጋ ለ8ኛ፣ለ10ኛ፣ለ12ኛ ክፍል የኦሮሞ ተማሪዎች አገር አቀፍ ፈተና ለሚወስዱ የተላለፈ ጠቅላላ መልዕክት በኦሮሞ ተማሪዎች ህብረት፣እንደሚታወቅ የቄሮ/ወጣቶች/ አገር አቀፍ ትግል



ፋክስ
FAX 0115-51-77-75
ፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1370
ስልክ
Tel. 0115-51-50-99
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa - Ethio

Scanned by CamScanner

እንቅስቃሴ በተማሪዎች እና በጠቅላላ በኦሮሞ ህዝብ ተጀምሮ 5 ወራት አልፎ ወደ 6ኛ ወር ተሻግሯል፣በዚህ ጊዜ በተደረገው እንቅስቃሴ የኦሮሞ ቄሮ እንቅስቃሴ ከፍተኛ እንደነበር ይታወቃል። በነዚህ ወራት ውስጥ የአጋዚ ጦር በ1000 የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆችን በጠራራ ፀሀይ በጥይት ገድሏቸዋል በሚል (ጥራዝ 10)፣ አለም አዱኛመ አንድነት ሀይል ነው ሀይል አንድነት ነው፣ በወያኔ ጦር ውስጥ በተለያዩ ደረጃ የምትገኙ የኦሮሞ ልጆች በተለይም በፓሊስ፣ በሚኒሻ፣ በአድማ በታኝ እና የሀገር መከላከያ ሰራዊት ውስጥ ለሚገኙ በሙሉ ባላችሁበት ተደራጅታችሁ የኦሮሞ ለነጻነት ጦር እና ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ሆናችሁ ወያኔን ከስልጣን ለማውረድ እንድትበረታቱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን በሚል፣ አለም አዱኛ በቄሮ (ወጣቶች) ነሐሴ 17፣ቄሮ ቢሊሱማ (ወጣቶች ለነፃነት) ኦሮሞ በወቅታዊ ጉዳይ ጸረ-ባርነት ትግል ላይ የሰጠው መግለጫ በሚል፣ሞይካ ሞይቦን ነሐሴ 16፣ዲናዲግ (ጠላትን በትን) ለታቦሬ ነሐሴ 16፣ዲናዲግ ለታቦሬ፣ነሐሴ 16፣ ዲናዲግ ለታቦሬ፣ ለተሾመ፣የቄሮ ሰላምታ ይቅደም ነሀሴ 14 በሚል፣ አደአ ቢሊሱማ ኦሮሞ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አርማ፣ ታቦሬ የልጁ ደም ፈስሶ አይቀርም ኦሮሚያ ነፃ ትወጣለች፣ ታቦሬ ወጋ የቄሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ ለኦሮሞ ህዝብ ያስተላለፈ መልዕክት በሚል፣ ዲና ዲግ ለተሾመ ለቄሮ ድምጽ የሚያስፈልግ መ[illegible]ዎች ነሐሴ 5 በሚል፣ ዲና ዲግ ነሐሴ 4 ለታቦሬ ወጋ፣ታቦሬ ወጋ ነሐሴ 3 ቄሮ ቢሊሱማ በያዘው ዓላማ በኦሮሚያ ውስጥ በፀረ-ባርነት ትግል ቀጠሮ ሳይዝ ባልታወቀ ጊዜ እና ቦታ በወያኔ ጦር ላይ ፈተና በመሆን ፀረ-ባርነት ትግል ይቀጥላል በሚል /ጥራዝ 5/፣ ዲና ዲግ ለታቦሬ፣ ታቦሬ ለዲና ዲግ፣ዲና ዲግ ለኢጃራ ዩሚዩ፣ ቄሮን /ወጣትን/ እስራት ወደኃላ አይመልሰውም፣በመጨረሻ የተሰጠ የምስጋና መልዕክት፣የኦሮሞ ትግልና የቄሮ ነፃነት እንቅስቃሴ ታሪክ፣ወደ ኦሮሚያ ለመመለስ ሲደረግ የነበረው ጥረት የ1ኛ ዙር ጉዞ በሚል (ጥራዝ 2)፣ አርማ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ የፈሰሰው ደምና የረገፈው ነፍስ ባህር ሆኖ ጠላትን ይጠርጋል፣ በስደት ከሀገር ውጭ ያላችሁ የኦሮሞ ልጆች፣የኦሮሞ ትግል፣ ዲና ዲግ ለኦዳ፣ኬይሮን ደረጄ፣ከባሬንቱ ገዳ፣ በሚል (ጥራዝ 3)፣ በዩኒቨርስቲ ቄሮ በኩል የተገባ ቃል፣የሞኝ ሳቅ አይደበቅም፣ ድል ለኦሮሞ ህዝብ ለታቦሬ ወጋ፣ድል ለኦሮሞ ህዝብ ኦሮሚያ ነፃ ትወጣለች ከታቦሬ ወጋ ለዲና ዲግ፣ታቦሬ ወጋ ግንቦት 19 ሱቱማራጋ፣ ታቦሬ ወጋ ግንቦት 18፣ ዲና ዲግ ግንቦት 18 በሚል ጥራዝ 9 ለታቦሬ፣ ታቦሬ ወጋ ሀምሌ 27



Scanned by CamScanner

ቁጥር ______
Ref.No
ቀን ______
Date

መብቱን እስኪያስከብር እና ነፃነቱን እስኪቀዳጅ ድረስ የመጨረሻውን የመስዋዕትነት ትግል ከማድረግ ወደ ኋላ መመለስ አይኖርም፣ ታቦሬ ወጋ ሀምሌ 27፣ የኦሮሞ ነፃነት ቄሮ ድምጽ ማስታወቂያ፣የነጻነት ቄሮ ድምጽ ሬድዮ የኦሮሞን ህዝብ ለማገልገል ዝግጅቱን አጠናቅቋል ታቦሬ ወጋ ሀምሌ 28 የኦሮሞነት፣የወገን እና የወንድማማችነት ጥሪ፣ታቦሬ ወጋ ከተለያዩ የኦሮሚያ ጽ/ቤት መዋቅሮች ዛሬ የደረሱ ዜናዎች ሀምሌ ወር በሚል (ጥራዝ 6)፣ ታቦሬ፣ ዲና ዲግ ለታቦሬ ህዳር 15፣ አለም አዱኛ ህዳር 13 ቄሮ ያልተለመደ፣ ዲና ዲግ ለኢጃራ ዩሚዩ፣ ዲና ዲግ ህዳር 10 ለታቦሬ ፣ ኦዳ፣ ቄሮ፣ኤችዩ፣ታቦሬ ወጋ ህዳር 6 ለብሄር ነፃነት የፈሰሰው ደም በፖለቲካዊ ስልጣን ጥቅም አይሸራረፍም በሚል (ጥራዝ 1)፣ ታቦሬ ወጋ ለኦሮሞ ወጣቶች ጥናትና ምርመራ፣ የኦሮሞ ወጣቶን ግራ እያጋባ ያለው ምን አይነት ችግር ነው ወዘተ፣ ዲናዲግ  በማንኛው ጊዜ ለታቦሬ ወጋ፣ ዲናዲግ ለገዳ፣ ታቦሬ አጀብ አጀብ በሚል (ጥራዝ 7)፣ ታቦሬ ወጋ ሰኔ 26 አምስተኛ ዙር ፀረ ባርነት ትግል በምስራቅ ኦሮሚያ ለጨቋኝ ወያኔ መንግስት አሳሳቢ በሆነ ሁኔታ የቀጠለ መሆኑ፣ ዲና ዲግ ሰኔ 25 ለታጋሬ፣ ዲና ዲግ ሰኔ 24. በኦሮሞ ልጆች ላይ እየተፈጸመ ያለው ግድያ የጸረ ባርነት [illegible] [illegible] አይመልሰውም ከቄሮ ቢሊሱማ (ከወጣቶች ለነፃነት) ኦሮሞ የተሰጠ አጭር መግለጫ፣ታቦሬ ወጋ ሰኔ 22፣ዲና ዲግ ሰኔ 22 ለኢጃራዩሚዩ፣ ዲና ዲግ ሰኔ 17 ለታቦሬ የኦሮሞ ወጣቶች የወያኔ ጦር መረማመጃ መሆን የለባቸውም በሚል (ጥራዝ 8)፣ የኦሮሞ ህዝብ የትግል ተቃውሞ በጋሮምሳ ዋቀሳ አንብብና አስተሳልፍ፣በቤካ ኢረና የኦሮሞ ህዝብ ትግል መግቢያ፣ የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ አምባገነን መንግስት ፊንፊኔን ከታላቁ ኢትዮጵያ ጋር የማደባለቅ፣ ዲና ዲግ ለኦዳ መስከረም1፣ ታቦሬ ለዲና ዲግ መስከረም 1፣ዲናዲግ ለኦዳ ጳጉሜ 2፣ የኦሮሞ የነፃነት ቄሮ ድምጽ ዲናዲግ ጳጉሜ 1 ለታቦሬ ልዩ፣ ተነሱ የኦሮሞ ህዝብ፣ ብሄራዊ ንቅናቄ ሳይቋረጥ 9 ወራት በላይ በመላው ኦሮሚያ ውስጥ ሲቀጣጠል የነበረው የወያኔ መንግስት በስጋት ውስጥ ገብቷል በሚል (ጥራዝ 4)፣ በሚል ሲፃፃፍና ህዝቡ ለአመጽ ሲያነሳሳ የነበረ በመሆኑ፣

4ኛ ተከሳሽ ኢፍ ገመቹ

- መስከረም ወር 2007ዓ.ም ቀኑ በውል ተለይቶ በማይታወቅበት በግርማ ጥሩነህ /አብዲ/ በተባለ ግለሰብ አማካይነት ለኦ.ነ.ግ. አባልነትና ለሰገሌ ቄሮ/የኦነግ ወጣቶች ድምጽ/ለመስራት የተመለመለ በመሆኑ፡-



Scanned by CamScanner

ቁጥር_______________
Ref.No
ቀን_______________
Date

- ጥቅምት 3/2007 ዓ.ም በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ግፍ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየፈጸመ ነው፣በሚል ለመጀመሪያ ጊዜ የሰገሌ ቄሮ የዜና ገጽ ላይ ዜና ያነበበ ሲሆን በዩንቨርስቲዎች ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ እየተካሄደ ነው፣ ማስተር ፕላኑ ከፍተኛ ብጥብጥ አስከትሏል ወዘተ በሚል አፍራሽ ዜናዎችን በማንበብ የጀመረ ሲሆን ይህንኑ ድርጊት በሳምንት ለሶስት ቀናት አንድ ቀን በአማሪኛ ሁለት ቀን በኦሮምኛ ለአመጽና ለብጥብጥ የሚቀሰቅሱ ጽሁፎችን በማዘጋጀት በሰነድ ማስረጃው ላይ በተጠቀሱት የኢ ሜይል አድራሻ በመጠቀም በኢንተርኔት አማካኝነት ውጭ ሀገር ላሉ የሰገሌ ቄሮ አመራሮች በመላክ በዩትዩብ እየተለቀቀ ህዝቡ ለአመጽና ለብጥብጥ እንዲወጣ ሲአደርግ የቆየ በመሆኑ፣
- በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች ለሰልፍ በመውጣታቸው ምክኒያት ተደበደቡ፣የኦሮሞ አርሶአደሮች መሬታቸውን ተነጠቁ፣የኦሮሞ ህዝብ በግፍ እየታሰረ ነው በማለት ዜናዎችን በማዘጋጀት በላፕቶፕ ይህንኑ ዜና በመቅረጽ በግርማ ጥሩነህ /አብዲ/ አማካይነት ውጭ ላሉ የኦ.ነ.ግ አመራሮች በኢሜይል በመላክ በዩቲዩብ መበልቀቅ እስከ 2007 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በዚህ ተግባሩ የገፋበት ሲሆን በመሃል ግርማ ጥሩነህ /አብዲ በመታሰሩ ምክንያት የተቋረጠውን የሰገሌ ቄሮ ድምጽ በድጋሚ በያዘው ክበበው አማካኝነት እንዲቀጥል ተደርጎ አውስትራልያ ከሚገኘው የሰገሌ ቄሮ አስተባባሪ ጫቶ በኢሜል ስሙ ታቦሬ ወጋ ለተከሳሹ ኢፋ ገመቹ ስልክ በመደወል የተጀመረውን የሰገሌ ቄሮ ስራ በመጠቀም ህዝቡን ለአመጽና ለብትብጥ የማነሳሳት ተግባሩን ከአልያድ በቀለ ጋር ማስቀጠል እንዳለባቸው ትዕዛዝ በመቀበል በድጋሚ ስራውን በማስፋት የቀጠለበት በመሆኑ፣
- በቴክኒክ ማስረጃው ላይ በተገለጹት የስልክ ቁጥሮች በመጠቀም በ17/05/09 ዓ.ም ውጭ አገር ስነበረው ለጋሹ ለሚሳ /ታቦሬ ወጋ/ /ጫቶ/ ለተባለው የኦነግ አመራር የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ /የሰገሌ ቄሮ ድምጽ የሬዲዮ ስርጭት ለመጀመር ሁኔታዎችን እያመቻቸ እንደሚገኝ በመጥቀስ ስርጭቱ በአማርኛና በኦሮሚኛ ቋንቋዎች እየተዘጋጀ በሳምንት እንደሚሰራጭ፣ በኢሜይል አድራሻው ጋሹ ለሚሳ/ታቦሬ ወጋ/ጫቶ የላከለት የኦ.ነ.ግ ስትራቴጂ እንደደረሰው በመጥቀስ ያሶ ከበኮ የተባለው የኦ.ነ.ግ አባል ኦ.ነ.ግ ቀደም ሲል የሚያራምደውን አላማ መቀየር አለበት የሚል አስተሳሰብ ቢያራምድም ጠንካራ እንቅስቃሴ እያደረገ እንደሚገኝ ለኦሮሞ ህዝብ አለኝታ የኦ.ነ.ግ የትጥቅ እንቅስቃሴ መሆን እንዳለበት ይህንን አጠናክሮ ማስቀጠል ያለበት በአገር ውስጥ ያለው የኦሮሞ ወጣቶች መሆናቸው ተከሳሽ ኢፋ ገመቹ /ሃሪሮ/ለጋሹ ለሚሳ የገለጸለት በመሆኑ፣
- ህዳር ወር 2008 ዓ.ም ጋሹ ለሚሳ /ጫቶ/2500 የአሜሪካን ዶላር ከውጭ አገር ለተከሳሹ ልኮለት ከኦሮሚያ ኢንተርናሺናል ባንክ ጉለሌ ቅርንጫፍ ተቀብሎ ላፕቶፕ በመግዛት የሰገሌ ቄሮን ህዝቡን ለአመጽና ለብጥብጥ የመቀስቀስ ተግባሩን አጠናክሮ የቀጠለበት በመሆኑ፣



Scanned by CamScanner

- በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በቡራዩ ከታ ሃይፐርቴንሽን/ወለጋ ሰፈር/ ቤት ክሌሎች ተከሳሾች ጋር ተከራይተው ኢፋ ገመቹ /ተከሳሽ/ የሰገሌ ቁሮ ዜና ኤዲተርና ተቆጣጣሪ ፣አሊያድ በቀለ የሰገሌ ቁሮ ስራ አስኪያጅ የተዘጋጀውን ዜና ለጋሹ ለሚሳ/ጫቶ/በኢሜይል የሚልክ፣ኬሮን ደረጀ እና ሴና ሰለሞን የሰገሌ ቁሮን ዜና አንባቢ በመሆን ያለውን ሁኔታ በማጋጋል ላይ የነበረ በመሆኑ፣
- ለሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ ሎን /አርማ/ ቲሸርት አሰርቶ፣የቪዲዮ ክሊፕ አዘጋጅቶ እንዲልክና ፈንዲሹ የተባለ ግለሰብ ያዘጋጀውን የፖለቲካ መቀስቀሻ ዘፈን ለጋሹ ለሚሳ የላከለት ሲሆን ተማም መንዜሱ በሚል ስም 100 የአሜሪካን ዶላር ከውጭ አገር ተልኮለት 200 ቲሸርቶችን ቡራዩ ገዳሜ ማተሚያ ቤት ከይ ቁሮ /ወጣቶች ተነሱ/ የሚል ጽሁፍ የታተመበት በማሳተም ለወጣቱ ለማሰራጨትና ሁከትና ብጥብጥ ለማባባስ ሲንቀሳቀስ የነበረ በመሆኑ፣
- የተለያዩና በሰነድ ማስረጃው ላይ የተመለከቱትን ጽሁፎች ለአመጽ መቀስቀሻነት የተጠቀመባቸው፡- ፍርሃትም ይሸነፋል፣ የኦሮሞ ማእበል ማግስት፣ የመሳይ ከበደ በር፣ የአባይ ጸሀዬ ጦርነት፣ኦሮሞ በጦቢያ ስር ዜግነት አግኝቶ አያውቅም እና የመሳሰሉትን ጽሁፎች በማዘጋጀት ሁከትና አመጽ ሲቀሰቅስ የቆየ በመሆኑ
- ለአመጽና ብጥብጥ የሚያነሳሳ፣ ጸሃይ በሚል አልበም የተዘጋጀና ለታቦሬ ቦጋ/ጫቶ/ የተላከለት ሲሆን የሰገሌ ቁሮ ቢልሱማ አስተባባሪ በመሆን ይህንን የህቡእ ተግባር ለመፈጸም የገንዘብ ድጋፍ በመቀበል የኦነግን አላማ ለማስፈጸም ሲንቀሳቀስ የነበረ በመሆኑ በፈጸመው የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈጸም ማቀድ ማሴር ማነሳሳት ወንጀል ተከሰዋል።

## 2ኛ ክስ

## 2ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች ላይ ብቻ

## ወንጀል

በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ፣ለ፣38/1/ እና የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ፣

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በመላ ሀሳባቸው እና አድራጎታቸው በወንጀሉ ድርጊት እና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን፣ የሀገሪቱን ህዝቦች አንድነት ለመሸርሸር ዓላማ ይዞ እና አላማውን ለማስፈፀም እና ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት፣በመንግስት ላይ ተፅእኖ ለማሳደር፣የሀገሪቱን መሰረታዊ ፓሊቲካዊ፣ ህገ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር ___
Ref.No
ቀን ___
Date

መንግስታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይም ለማፍረስ ከሚንቀሳቀሰው እና ኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ ብሎ እራሱን የሚጠራው ሽብርተኝነት ድርጅት ውስጥ አባል በመሆን፣ በውጭ ሀገር ከሚገኙ የኦነግ አመራሮችና አባሎች ጋር በስልክ፣ በኢሜይል ግንኙነት በማድረግ ተልዕኮ በመቀበል፣የኦነግ ሰገሌ ቄሮ/የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የወጣቶች ድምጽ) ሚዲያ/ሬድዮ) በሚል በተቋቋመ ውስጥ ዜና አዘጋጆች፣ ዜና አንባቢዎች በመሆን በመደራጀት ህዝቡን ወደ አመጽና ረብሻ ውስጥ ገብቶ የሽብር ወንጀል እንዲፈጸም የቅስቀሳ ዘፈኖችን በመዝፈንና፣በማዘፈን አባላትን በመመልመልና በማደራጀት ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሲሆኑ በተለይም፡-

2ኛ ተከሣሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በሚያዝያ ወር በ2007 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን የኦፌኮ የፓለቲካ ድርጅት ተወካይ ታሪኩ ደሳለኝ በተባለው አማካኝነት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) በማለት እራሱን ለሚጠራው የሽብርተኛ ድርጅት ተመልምሎ አባል በመሆኑ፣

2ኛ ተከሣሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በሚያዝያ ወር በ2007 ዓ/ም ታሪኩ ደሳለኝ የተባለ የኦነግ አባል ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን ነቀምት ከተማ በተለምዶ ቦርድ ሰፈር ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ከተከሳሹ ጋር በመገናኘት በውጭ ሀገር የሚኖርና የኦነግ ሰገሌ ቄሮ ቢሊሱማ/የኦነግ ወጣቶች ለነፃነት/በሚል በተቋቋመው የኦነግ ሚዲያ ላይ የሚሰራና በውጭ ሆኖ የሚመራ የኦነግ አመራር ጋር የኢሜይል አድራሻውን እስጥሀለሁ መተዋወቅ አለብህ ብሎ ሲነግረው በሀሳቡ በመስማማት Taboree @hot mail. Com የሚል የኢ.ሜይል አድራሻ በመቀበል በተሰጠው አድራሻ አማካኝነት የኦነግ አመራር ከሆነው ጋሹ ለሜሳ (ጫቶ) ከተባለው ጋር ከተዋወቀውም በኃላ ሲሆን በመቀጠል በነቀምት ከተማ እና በአካባቢው ላይ የመንግስትን ማንኛውም እንቅስቀሴ እየተከታተልክ መረጃ በአድራሻዬ ትልክልኛለህ በማለት የኦነግ አመራር የሰጠውን ተልዕኮ የተቀበሉ አባል በመሆኑ፣

2ኛ ተከሣሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በታህሳስ ወር በ2008 ዓ/ም በውጭ ሀገር የሚገኙ የኦነግ አመራር የሆነው ጋሹ ለሜሳ /ጫቶ/ "ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን በነቀምት ከተማ አንተን ተክቶ መረጃ ሊሰጠን የሚችል ሰው መልምልና አስታውቀኝ" በማለት



Addis Ababa - Ethiopia

Scanned by CamScanner

ትዕዛዝ ሰጥቶት፣ትዕዛዙን በመቀበል አብዲ ጉተታ የተባለ ግለሰብ ውጭ ሀገር ላሉት ለኦነግ አመራሮች መረጃ እንዲያቀብል የመለመለው መሆኑ፣

2ኛ ተከሣሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በግንቦት ወር በ2008 ዓ/ም መጀመሪያ አካባቢ ውጭ ሀገር የሚገኘው የኦነግ አመራር የሆነው ጋሹ ለሚሳ /ጫቶ/ የተባለው ለተከሳሹ ስልክ በመደወል ከኦልያድ በቀለ (1ኛ ተከሳሽ) ጋር በመሆን የኦነግ ሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ (የኦነግ ወጣቶች ለነፃነት ድምጽ) የሆነውን ሚዲያ(ሬድዮ) በአዲስ መልክ ስራውን ማስቀጠል አለባችሁ"በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶት፣ትዕዛዙን በመቀበል የሚዲያ የዜና ስራ የሚያስቀጥል መሆኑን በኢሜይል አድራሻው ውጭ ሀገር ለሚገኘው ለኦነግ አመራር የገለጸለት በመሆኑ፣

2ኛ ተከሣሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በሚያዝያ ወር በ2008 ዓ/ም ኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ ከታ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ለሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ (ለኦነግ ወጣቶች ለነፃነት ድምጽ) ሚዲያ /ሬድዮ/ ስራ መስሪያነት በተከራዩ እስቱድዮ ዜና በማዘጋጀት ሪከርድ በማድረግ በ1ኛ ተከሳሽ አማካኝነት ውጭ ሀገር ለሚገኙ ጋሹ ለሚሳ /ጫቶ/ ለተባለ የኦነግ አመራር ለሆነው በኢሜይል አድራሻው በመላክ በእሱ አማካኝነት ሊተለለዩ ማህራዊ ድረገጽ እንዲሰራጩ በማድረግ ህዝቡ ለአመጽ እንዲነሳሳና የሽብር ወንጀል እንዲፈጸም ሲሰራ የቆየ በመሆኑ፣

2ኛ ተከሣሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በሚያዝያ ወር በ2007 ዓ/ም እስከ ህዳር ወር 2009 ዓ/ም መጨረሻ ላይ የኦነግ ሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ /የኦነግ የወጣቶች ለነፃነት ድምጽ) ዜና አንባብና የፕሮግራም አዘጋጅም በመሆን፣ ውጭ ሀገር ከሚገኙ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር እና አባሎች ጋር በሰነድ ማስረጃነት በገለጽነው አግባብ በፌስቡክ እና በኢሜይል በመጠቀም ህዝቡ ለአመጽ፣ ለብጥብጥ እንዲነሳሰና የሽብር ወንጀል እንዲፈጸም የሀሰት መረጃዎች በዜና መልክ በማዘጋጀት ሪከርድ በማድረግ ከሽብር ድርጅት አመራር ጋር ሲያፍ የነበረው፣ ታቦሬ ወጋ የኦሮሞ ነፃነት ወጣቶች ማብራሪያ ህዳር 29 ቀን 2008 ዓ/ም ኦሮሚያ በአሁኑ ጊዜ ያለችበት እና የወያኔ ጦር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚል፣ ምክንያት የሽብርተኝነት ጦር በአገሪቷ ላይ አስማርቶ በዘር ማጥፋት ዘመቻ ወንጀል እየሰራ ይገኛል በሚል ለሞይቡል ምስጋኑ በ5/4/2009፣ ሞይቡል ምስጋኑ 5/4/2009 የሞት፣አፍነው ማሰር፣ ተኩሰው ማቁሰል፣ ህገ ወጥ ፍተሻ እና የንብረት ዝርፍያ፣አስገድዶ መድፈር ጨምሮ ለሰው ልጅ ኑሮ፣ ተስፋና ሞራል



Scanned by CamScanner

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

የማይሰጡ ዘመቻ በኛ ህዝብ በኦሮሞ ላይ እየተፈጸመ ነው በሚል፣ ታቦሬ ወጋ ታህሳስ 4 ለሞይቡል ምስጋኑ 5/4/2009፣በሸገር ዞን የተለያዩ የምስራቅ አካባቢ ወረዳዎች ውስጥ ሰላማዊ የኦሮሞ ህዝብ በወያኔ ጦር ወደ እስር ቤት እያጓዙ ነው በሚል፣ታቦሬ ወጋ ታህሳስ 4 ሞይቡል ምስጋኑ 5/4/2009 የሚያስፈልጋችሁን ዜና ከተለያየ ቦታ በማምጣት እንዲመቻቹ ታቀናብራላችሁ በሚል፣ ውስኖችን ወደ እናንተ አላክንም በሚል፣ ታቦሬ ወጋ ታህሳስ 3 በመላ ሀገርቷ ውስጥ ወያኔ የሚጠቀሙት ዘዴ ለብቻ በዩኒቨርስቲ ተማር ላይ በተለይም በኦሮሚያ ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ በከፍቱት በኦሮሞ ላይ የሽብር ዘመቻ፣ የጭካኔና የግድያ፣ እስር፣ ልጃገረዶችና ሴቶችን በመድፈር ለሰው ልጅ የማይገባ ሰቃይ፣የውሸት ዶክመንተሪ በማቀናበር ዘመቻ ሁሉም ህዝብ ጋ የደረሰ መሆኑ፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲያሳልፉ አድርገዋል በሚል፣ ሞይቡል ምስጋኑ 5/4/2009 የነፃነት አላማ ወደ ኃላ ለመመለስና የህዝብን አይን ለመያዝ ባለህብት ላይ የእስር ዘመቻ በመክፈት በሚል፣ ገዳመጫ ታህሳስ 3 ለቤካን ገሬ ፊልማ ዲባ ገድቲ በሚል፣ የቱ ለማ ኦሮሞ ነፃነት ትግል ታሪክ አባገዳ ጋር በሚል፣ሚቹ ለሚ ታህሳስን የነቀምቴ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣በትላንትናው ቀን በጠላቶች መኪና ሰላም ባስ በሚባል ላይ በወሰደው እርምጃ የጠላቶች መኪና ከአዲስ አበባ ወደ አሶሳ የሚሄደውን ከስራ አገልግሎት ውጭ አድርጎታል በሚል፣ ዲናዲግ ነሐሴ ከነፃነት ኦሮሞ ወጣቶች ለኦሮሞ ህዝብ የተላከ መልዕክት፣ የአምባገነን ስርዓትንና አስጨናቂ ወያኔን ለማጥፋት የኦሮሞ አገር አባትነት ለማስከበር ከ2011 እ.ኤ.አ ጀምሮ የተጀመረው ትግል እየተጠናቀቀ ስለሆነ የውስጥ እና የውጭ ኦሮሞ አንድነትን ማጠናከር በሚል፣ ምዕቡል ምስጋኑ 5/4/2009፣ ገዳመጫ ታህሳስ 4 ለታቦሬ አዳ ቤካ ለምን እንጠላለፋለን በኖሌ ቡታ በሚል፣ የኦሮሞ ጠላቶች ዘዴ፣ የኦሮሞ ህዝብና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ማድረግ ያለባቸው ድርጅቱ የህዝብ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ከዚህ ቀጥሎ ባለው ነጥብ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ይሆን ዘንድ በየጊዜው ግንዛቤ እየሰጡ መሄድ ጥሩ ነው በሚል፣ ሞይቡል ምስጋኑ 5/4/2009 ዓ/ም የኦሮሞን ዘመቻ በማድረግ ኦሮሞን ለመከፋፈል ከምንቀሳቀስ በሚል፣ አንድ አገር ሀገር ለመባል እንደፓለቲካ ሳይንስ አራት ነጥቦች ተቀምጠዋል በሚል፣ታቦሬ ወጋ ህዳር 10 ሰላምታ ይትደም በሚል፣(ጥራዝ 13)፣

2ኛ ተከሣሽ የኦነግ ሰገሌ ቄሮ /የኦነግ የወጣቶች ድምጽ/ ሚዲያ/ሬድዮ/ዜና አዘጋጆችና ዜና አንባቢዎች በሚል የሽብር ቡድን ውስጥ በመደራጀት፣ የሽብር ቡድኑ የሥራ


ፋክስ
FAX 0115-51-77-75
ፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1370
ስልክ
Tel. 0115-51-50-99
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa - Ethi

Scanned by CamScanner

የሚውል ገንዘብ ከህዳር 1 ቀን 2008 ዓ/ም እስከ ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን በቡራዩ ከተማ ከታ አካባቢ በሚገኘ የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ኢማ ቅርንጫፍ ከውጭ ሀገር ከሚገኙ የኦነግ አባላት ከሆኑ 1ኛ ከብር አባትምቡል ከተባለው 22,213.16 ብር፣2ኛከማሪ ዋቅጅራ ከተባለው 21.982.89 ብር፣3ኛ ምስጋና ደሸከታ ከተባለ 21.655.68 ከውጭ የተላከለት ሲሆን፣ከጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 2008 ዓ/ም በቀን 31/12/2015 እ.ኤ.አ ከአዋሳ ቅርንጫፍ በራስ ስም ወደ እራስ የቁጠባ ሂሳብ ቁጥር (5/A-291549)፣ ሀያ ሺህ ብር/20,000) ገቢ ማድረጉን ከነቀምት ቅርንጫፍ የተገኙ መሆኑን፣

3ኛ ተከሳሽ ቀነኒ ታምሩ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀ በየካቲት ወር 2008 ዓ/ም መጀመሪያ አካባቢ በአዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ኤለፋንት ካፌ በሚባል ውስጥ ግርማ (በቅጽልስም አብዲ) ከተባለና ያባቱ ስም ያልታወቀ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) አባል ጋር በመገናኘት እስከ አሁን ያልነገርኩሽን ጉዳይ ልንገርሽ በማለት የኦነግ አባል በመሆን፣አዲስ አባላትን በመመልመል እና በማደራጀት፣ የኦነግ ድርጅት የሚሰጠውን ወታደራዊ እና ፓለቲካዊ ስልጠና በመስጠልን የኦነግ አባል በመሆን ትሰራለሽ ወይ? በማለት ያቀረበላትን ጥያቄ በመቀበል እና በሀሳቡ በመስማማት አባል በመሆኗ፣

3ኛ ተከሳሽ ቀነኒ ታምሩ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀ በየካቲት ወር 2008 ዓ/ም ኢጋማስ በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ወሎ ሰፈር ተብሎ በሚጠራ አካባቢ የሚገኙ ስሙ ያልታወቀ ካፌ ግርማ (ቅጽል ስም አብዲ) ከተባለ የኦነግ አባል ጋር በመገናኘት ቡና እየጠጡ ከቆዩ በኃላ "አንቺ ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ሻምቡ ከተማ በመሄድ ለጊዜው ብዛቱ ያልታወቀ በካርቶን ያለ የሚሰጥሽ ቦምብ ሄደሽ ታመጫለሽ፣ይህንን ጉዳይ ከፈፀምሽ በኃላ ለኦነግ አባልነት ወጣቶችን መልምለሽ በማደራጀት በኬንያ የሚገኙ ሶሎሎ ተብሎ በሚጠራ የኦነግ ማሰልጠኛ ይዘሻቸው ትሄጃለሽ በማለት ተልዕኮ ሰጥተዋት፣ የተሰጣትን ተልዕኮ የተቀበለች እና በሀሳቡ የተስማማች በመሆኗ፣

3ኛ ተከሳሽ ቀነኒ ታምሩ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀ በመጋቢት ወር 2008 ዓ/ም መጀመሪያ ላይ አዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ አትና ሲኒማ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ገርጊዶ የተባለች ያባቷ ስም ያልታወቀ የኦነግ አባል ከሆነችሁ ጋር በመገናኙት በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን ደንቢደሎ አካባቢ ባንቺ ስር የሚገኙ የኦነግ አባሎች በም[illegible] ላይ

እንደሚገኙ እና ምን እንደሚያስፈልጋው ጠይቃት፣ተከሳሿ በበኩሏ በስሯ በደንቢ ዶሎ አካባቢ የሚገኙ የኦነግ አባሎች አመጽ በማነሳሳት መንገድ በመዝጋትና የህዝ-ወጥ ሰልፍ በማድረግ ላይ እንደሆኑና ለጊዜ የጦር መሣሪያ፣ በምብ እና ገንዘብ እንደሚያስፈልጋቸው በመጠቆም፣ ገርጌደ የተባለችውም የኦነግ አባል የሚያስፈልጋቸው በዝርዝር በዕቅድ መልክ እንዲታቀርብ የገለፀችላት በመሆኑ፣

3ኛ ተከሳሽ ቀኑ ባልታወቀ ሚያዝያ ወር 2008 ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ አጎና ሲኒማ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በሚገኙ የጀበና ቡና በሚጠጣበት በረንዳ ላይ ገርጌዶ ከተባለች የኦነግ አባል ጋር በመገናኘት ለአነግ አባልነት ከአሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ከደንቢ ዶሎ አካባቢ የመለመለቻቸውን 1ኛ ቃሉዊ ለሜሳ፣2ኛ አበራ በዳዳ፣3ኛ አበበ ጀለን፣4ኛ ለሚ ወርቅነህ፣5ኛ ሰቦቃ የአባቱ ስም ያልታወቀ፣6ኛ ቢቂላ ታቦር፣7ኛ ጋዲሳ ጨዋቂ የተባሉትን የኦነግ አባል ስምና ስልክ ቁጥራቸውንም ጭምር የሰጠቻት በመሆኑ፣

3ኛ ተከሳሽ ቀኑ ባልታወቀ በግንቦት ወር 2008 ዓ/ም ኢፋ ገመቹ (2ኛ ተከሳሽ) የኦነግ ሰገሌ ቄሮ አባል አማካኝነት ከ1ኛ ተከሳሽ ኦልያድ በቀለ ጋር በስልክ ተዋውቀው እንዲተዋወቁ ያደረጋ ሲሆን ተዋውቀው ከቆዩ በኃላ በነሐሴ ወር 2008 ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ ከታ አካባቢ በሚገኙ ዳሚቱ ካፌ በሚባለው ውስጥ በመገናኘት ቡና አዘው እየጠጡ እያሉ 1ኛ ተከሳሽ በስሞኑ ስራ ከኛ ጋር ትጀምሪያለሽ፣ የስራው አይነትም የሰገሌ ቄሮ (የወጣቶች ድምፅ) የሚል የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ሚዲያ ነው የምንሰራውም ስራ የፓለቲካ ስራ ነው፣ በሳምንት ሶስት ቀን /3/ ብቻ ነው የምትሰሪው፣ የኦነግ ሰገሌ ቄሮ ሬድዮ ዜና አንባቢ እና ቃለ መጠየቅ ስራዎችን ትሰሪያለሽ በየወሩ 3000/ ሶስት ሺህ/ ብር ይከፈልሻል በማለት ያቀረበላትን ሀሳብ በመቀበልና ወደ ስራው የገባች በመሆኗ፣

ቀኑ በትክክል ባልታወቀበት መስከረም ወር 2009 ዓ/ም 1ኛ ተከሳሽ በ0960235635 በሆነው ስልክ ቁጥር ለተከሳሿ/ለቀነኒ ታምሩ/ ደውሎለት ኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን በቡራዩ ከተማ ከታ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በሚገኙ የሰገሌ ቄሮ /የወጣቶች ድምጽ/ እስቲድዮ ተቀጣጥረው በመገናኘት ዛሬ የምትሰሪው ስራ ሰጥሻለሁ በማለት በኦሮሞኛ ቋንቋ በኮምፒተር የተፃፈ ጽሁፍ ወደ አማረኛ ሲተረጎም ይዘቱም ይህ የሰገሌ ቄሮ /የወጣቶች ድምጽ) ሬድዮ በቀጥታ ከኦሮሚያ የሚተላለፍ ዜና፣ ልዩ ፕሮግራም እና ሙዚቃ የሚተላለፍበት ነው፣



Scanned by CamScanner

ፕሮግራሙን ስለተከታተላችሁ እናመሰግናለን፣ በተመሳሳይ ፕሮግራም እስከምንገናኝ በደህና ቆዩ፣ የሚል እንድታነበው ስጥቷት የተሰጣትን ጽሁፍ አንብባ እንደጨረሰች፣ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ካሉት ነዋሪዎች ጋር ቃለ መጠየቅ አድርገሽ ታቀርብያለሽ በማለት ከ1ኛ ተከሳሽ ተልዕኮ ተሰጥቷል፣ ተልዕኮውን ተቀብላ በተሰጣት ተልዕኮ መሰረት ሲትፈጽም የቆዬች በመሆኗ፣ 3ኛ ተከሣሽ ቀኑ በትክክል ተለይቶ ባልታወቀበት በመስከረም ወር 2009 ዓ/ም አብዲ የተባለ የአባቱ ስም ያልታወቀ የኦነግ አባል የሆነውን ቡራዩ ከተማ ከታ አካባቢ በሚገኘው ዳሚቱ ካፌ በሚባልውስጥ አግኝታው፣በኦሮሚያ ክልል ደምቢ ዶሎ ከተማ አካባቢ የኦነግ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? በሚል ቃለ መጠይቅ አቅርባለት፣ እስ የመጣው ከነቀምት ከተማ መሆኑን፣ በምስራቅ ወለጋ ዞን በነቀምት ከተማ ትግሉ የቀጠለ መሆኑ፣ የኦሮሞ ህዝብ ከኦነግ ጋር ያለ እንደሆነ የገለፀላት ሲሆን፣ ጫላ የተባለ ያባቱ ስም ያልታወቀ የኦነግ አባል ከዚህ በላይ በተገለጸ ጊዜ ቦታ እና በተመሳሳይ ይዘት ያለውን ቃለ መጠየቅ አቅርባለት፣ ከኦሮሚያ ክልል ከነቀምት ከተማ የመጣ መሆኑን፣የኦሮሞ ህዝብ ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ ጋር ያለ፣ መሆኑን የገለፀላት ሲሆን፣ ኦሮሚያ ክልል ቀለም ወለጋ ዞን ሰዬ ወረዳ በደምቢ ዶሎ ከተማ የሚኖሩ ቃለዊ ለሜሳ እና መኮንን የተባለ የአባቱ ስም ያልታወቀ የኦነግ አባሎች ለሆኑት 0917840115 በሆነ ስልክ ቁጥር ቃለዊ ለሜሳ በሚጠቀምበት 0917455336 በሆነው ስልክ ቁጥር ደውላለት "በኦሮሚያ ክልል ደምቢዶሎ ከተማ አካባቢ የኦነግ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል በሚል ቃለ መጠየቅ አቅርባለት፣ በደምቢ ዶሎ ከተማ ህዝቡ ለአመጽ የወጣ መሆኑን፣ በከተማ ውስጥ ያለው ሱቆች የተዘጉ መሆኑን የገለፀላት ሲሆን፣ መኮንን የተባለ ያባቱ ስም ያልታወቀ ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ቃለመጠየቅ አቅርባለት፣ የኦነግ አባሎች በደምቢ ዶሎ ከተማ ውስጥ ህገወጥ ሰልፍ እና የአመጽ እንቅስቃሴ ለማካሄድ ላይ እንደሆኑ፣ በደምቢ ዶሎ ከተማ ውስጥ ሱቅ ያላቸው ባለሀብቶች እንድዘጉ በኦነግ አባሎች እየተቀሰቀሱ መሆኑን፣ ውጭ ሀገር የሚገኙ የኦነግ አመራር በተሰጠው ትዕዛዝ/ መሰረት ህዝቡ ከቤት ውስጥ ባለመውጣትና የስራ አድማ በማድረግ ላይ የሚገኙ መሆኑን፣ የፌዴራል መንግስት ኦሮሞን በማፌናቀል በኢንቨስትመንት ስም ለጋምቤላ እና ለትግራይ ተወላጅ ለሆኑት መሬት እየተሰጣቸው ይገኛል በሚሉና ሌሎችንም ሰዎች ቃለ መጠየቅ በማድረግ በሞባይል ሪከርድ አድርጋ ለ1ኛ ተከሳሽ እያቀረበች የቆየች በመሆኗ፣ በከተማ ውስጥ አንዳንዱ እርምጃ መውሰድ የሚችሉ ሰዎች ስላሉና ስራውን

የመከራት ፍላጎት ያላቸው ሌሎች ሰዎች ካሉ እንዲያገናኙት፣ እርሟሽ የሚወስደበትን ሰው ከሱድን አባላት ጋር በመሆን ተወያይተው ወደ ተግባር ስራ እንደሚገቡ አዲስ አበባ ከተማ የነበረችው 3ኛ ተከሳሽ (ቀነኒ ታምሩ) የአመጽ አስተባባሪ የሆነችው በ4/13/2008 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ዞን ደምቢ ዶሎ ከተማ ለነበረው መኮንን ለተባለ ለኦነግ አባል ገልፃለት፣መኮንንም በበኩሉ ቀደም ሲል ከገናኛቸው የነበሩት ሰዎች ጋር ተገናኝቶ ከተወያየ በኋላ እንደሚያሳውቃት ገልጾላታል። ለአንድ ሳምንት ያህል ከቤት ሳይወጡ ያደረጉት አድማ እና በዚያ አድማ መነሻነት የሞተ ሰው ካለ፣ እንዲሁም ማህበራዊ አገልግሎት እንዳይሰጡ መመሪያ ያስተላለፈ የመንግስት አካል ወይም እራሱ ህዝቡ በራሱ ተነሳሽነት ያደረገው ተቃውሞ መሆኑን አዲስ አበባ የነበረችው 3ኛ ተከሳሽ ቀነኒ ታምሩ የተባለች የአመፁ አስተባባሪ በ2/1/2009 ዓ/ም በ0917840115 በሆነው ስልክ ቁጥር ኦሮሚያ ክልል ደምቢ ዶሎ ለነበረው መኮንን ለተባለ ያባቱ ስም ያልታወቀ የኦነግ አባል ለሆነው ደውላለት የጠየቀችው ሲሆን መኮንን የተባለ የኦነግ አባልም በበኩሉ ኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን የተደረገው አድማ በህዝቡ በራሱ ተነሳሽነት እንደሆነ፣ በከተማ ውስጥ ያሉ ሱቆች መዝጋትና የመሳሰሉት ተግባሮች ሲከናወኑ እንደነበሩና የሁለት ሰው ህይወት በአድማው እንደሞቱ የገለጸላት በመሆኑ፣

3ኛ ተከሳሽ ቀነኒ ታምሩ በየካቲት 7 ቀን 2009 ዓ/ም ላይ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ማዕከል በመቅረብ የራሷ መጠቀሚያ ሞባይል ተይዞ ሲፈተሽ ከሚሞሪ ውስጥ ከተከሰሰችበት የሽብር ወንጀል ጋር ግንኙነት ያለው (run for oromo protest) የኦሮሞ ተቃውሞ እንቀጥላለን፣ በሚል ይዘቱ በቪድዩ ሙዚቃ ላይ በኦነግ ባንዴራ የተቀነባበረ፣ በእሬቻ በዓል ላይ (Down Down woyane) የወያኔ ይውደቅ፣ የጦር መሣሪያ ይዞ ፍርሃት የለም እንፈራም በሚል የተዘፈነ፣ አትሳቁ አንስቅም በሚል፣ የኦነግ ባንዴራ በማውለብለብና በመያዝ ህዝቡን ለመቀስቀስና ለማነሳሳት የተዘጋጀ፣ የኦነግ ባንዴራ ያለው ቲሸርት በመልበስና በማቀነባበር ህዝቡን ለማነሳሳት የተዘፈኑ የተለያዩ ዘፈኖች የያዘ፣በመጠቀሚያ ሞባይል ሚሞሪ ውስጥ ህዝቡ ወደ አመጽና ረብሻ ውስጥ እንዲገባና የሽብር ወንጀል እንዲፈጸም አመጽ ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው በሞባይሏ ውስጥ የተገኙ በመሆኑ፣

5ኛ ተከሳሽ ባይሉ ነጮ

- የተለያዩ የኦነግ አመራሮች በሚሰጠን መመሪያ መሰረት በአገር ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ቃለመጠይቅ በማድረግ እና መረጃዎችን በማሰባሰብ ፕሮግራሞችን ለኦነግ በማዘጋጀት በላፕቶፕ በመቅረጽ የተቀረጹትን ዜናዎችና የኦነግ ፕሮግራሞች እንዲሁም ቃለ መጠይቆች ውጭ ለሚገኙ የኦነግ አመራሮች በእኔ ኢሜይል አድራሻ በመላክ እነሱ በዩቲዩብ ማህበራዊ ድህረ ገጽ ይለቁታል የምንሰራው ስራ ይህ ነው ብሎ ኦሊያድ በቀለ ባቀረበለት ሃሳብ የተስማማ በመሆኑ፣
- 2008 ዓ.ም በኦሊያድ በቀለ አማካይነት የኦ.ነ.ግ አባል በመሆን የተመለመለና የሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ ዜና አንባቢ እና የፕሮግራም መሪ በመሆን ሲሰራ የነበረ ሲሆን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ሚዲያ በሆነው ሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ በዜና አንባቢነትና በፕሮግራም መሪነት መስራት የጀመረው ሚያዚያ 2008 ዓ.ም ጀምሮ የሐሰት ዜናዎችን ሲያነብና ይህንኑ ፕሮግራም ሲመራ የነበረ በመሆኑ
- በኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከታ ቤት በመከራየት ከሌሎች ተሳሾች ጋር በመሆን የሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞን ህዝቡን ለአመጽና ለብጥብጥ የማነሳሳት ተግባሩን ለማስቀጠል ውጭ አገር ካሉ የኦ.ነ.ግ አመራሮች የገንዘብ ድጋፍ በመቀበል በወር 3000 ብር እየተከፈለው ሲሰራ የቆየ በመሆኑ፣
- በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በኩል በእ.ኤ.አ 18/08/2016 የ10964 ብር ከጌትነት ጀቤሳ ከአሜርካን አገር የተላከለትን ገንዘቡን ለአመጽና ብጥብጥ መቀስቀሻ ተግባሩ የተጠቀመበት በመሆኑ፣
- በ05/09/09 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ገፈርሳ የመኖሪያ ቤት ቁጥሩ 2699 ከአቶ ጋረደው ጉርሙ ላይ በወር 4000 ብር የ3ወር 12000 ከፍሎ በዚህ ቤት ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን ህዝቡን ለአመጽና ለብጥብጥ ሲቀሰቅስ የቆየ በመሆኑ፣

6ኛ ተከሳሽ ሴና ሰለሞን

- ከታህሳስ 2007 ዓ፣ም ጀምሮ የኦ.ነ.ግ አባልና የሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ/የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የወጣቶች ድምጽ/ በዜና አንባቢነት ስታገለግል የቆየች ሲሆን ለዚህ ተግባር በግርማ ጡሩነህ/አብዲ/ የተመለመለች በመሆኗ፣
- በሳምንት ለሶስት ቀናት የሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ ዜናዎችን በማንበቧ በወር 3000 ብር ሲከፈላት የቆየች በመሆኗ፣
- ጥቅምት 2009 ዓ.ም የኦሮሞ ህዝብን ለአመጽና ለብጥብጥ የሚቀሰቅስ ፊልም እየሰራች መሆኗን በመግለጽ ገንዘብ እንዲላክላት የኦ.ነ.ግና የሰገሌ ቁሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ የውጭ አመራር ለሆነው ለጋሹ ለሚሳ/ጫቶ/ታቦሬ ወጋ የጠየቀች በመሆኗ፣
- ለአመጽና ብጥብጥ የሚያነሳሱ የተለያየ ይዘት ያላቸውን በተናቀሳቃሽ ምስል የታጀቡ ዘፈኖችን በመዝፈን በዩቲዩብ የለቀቀች በመሆኗ፣
- የተለያዩ ለአመጽና ለብጥብጥ የሚያነሳሱ ጽሁፎችን በማዘጋጀት በኢሜይል አድራሻዋ ስትለዋወጥ የቆየች በመሆኗ፣
- ኦ.ነ.ግ ያወጣውቸውን መግለጫዎች በሰነድ ማስረጃው ላይ በተመለከቱት በኢሜይል አድራሻዋ ስትለዋወጥ የቆየች በመሆኗ ለአብነት ያክል በቀን 05/03/09 የኦሮሞ

አመራሮች የእርዳታ ጉባኤ በሚል የሚጀምር የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መግለጫን፣ከግብጽ የተሰጠን የኦሮሞ አንድነት የአቋም መግለጫ ፣ በቂሊንጦ ማረሚያ ቤት በደረሰ እሳት ቃጠሎ 67 ሰዎች ተገደሉ በሚል የሚጀምር ጽሁፍ፣እ.ኤ.አ 02/10/2016 የወጣን የኦነግ መግለጫ ‹የወያኔ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስርአቱን ስልጣን ላይ ለማስንበት የሚደረገው የመጨረሻው ጥረት›፣ወዘተረፈ የመሳሰሉትንና በሰነድ ማስረጃው ላይ የተገለጹትን ስትለዋወጥ የቆየች በመሆኗ፣

7ኛ ተከሳሽ ኤሊያስ ክፍሉ

- ለአመጽና ለብጥብጥ የሚያነሳሱ ዘፈኖችን በመዝፈንና ለሌሎች ተመሳሳይ አመጽና ረብሻ የሚቀሰቅሱ ዘፈኖችን ለሚዘፍኑ ዳይሬክት በማድረግ በዩቲዩብ በመልቀቅ ሁከታና ብጥብጥ ሲቀሰቅስ የቆየ በመሆኑ፣
- የካቲት ወር 2007 ዓ.ም ጥያቄ በሚል ርእስ በኦሮሚኛ ቋንቋ የተሰራ ተንቀሳቃሽ ምስል ያለበት የዘፈን ክሊፕ በማውጣት በዩ ቲዩብ የለቀቀ በመሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም በኦሮሞ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ያለው ጭቆናና ግፍ ማስቆም አለብን የኦሮሞ ህዝቦች ብዛታችን አሸዋ ነው ነገር ግን ፍቅርና ሰላም የለንም ሞት መቼም ቀኑ አያልፍም ስለዚህ ጭቆናን ማስቆም አለብን ከእኛ በፊት የነበሩ የኦሮሞ ጀግኖች ለእኛ ሲሉ ሞተዋል ለምን እኛ ወጣቶች ዝም ብለን እንቀመጣለን እያለ የኦሮሞን ህዝብ ለብጥብጥና ለአመጽ የሚያነሳሳ ዘፈን ያወጣና በዩቲዩብ የለቀቀ በመሆኑ፣
- ሰኔ ወር 2008 ዓ.ም በሰነድ ማስረጃው ላይ በተጠቀሰው የተከሳሹ የሚሜል አድራሻ /ona/ እና የሚል የኢሜያል ቡድን በመቀላቀል በቡድኑ የሚላኩለትና መልእክት ሲቀበል የቆየ በመሆኑ ለአብነትም የኦሮሞ ደም ፈስስ አይቀርም፣የኦነግ መግለጫ፣ዶ/ር መራራ ጉዲና ከእስር ይፈቱና ሌሎችም መልእክቶችን ሲቀበል የቆየና ይህም በሰነድ ማስረጃዝርዝር ላይ የተገለጸ በመሆኑ፣
- ከማል ኢብራሂም የተባለ በአሜርካን አገር የሚኖር የኦ.ነ.ግ አባል በገንዘብ የደገፈው በመሆኑ፣
- በ08/05/09 ዓ.ም 643 የአሜርካን ዶላር በኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ በኩል ተልኮለት የተቀበለ በመሆኑ፣
- ጥቅምት 100 የአሜሪካን ዶላር እና ህዳር ወር 2009 ዓ.ም 250 የአሜርካን ዶላር ሳምሶን ማርቆስ በተባለ ግለሰብ ተልኮለት ገንዘቡን ለዚሁ ለአመጽና ብጥብጥ ማነሳሻ የተጠቀመበት በመሆኑ፣

በጠቅላላው ተከሳሾች የኦ.ነ.ግ ሰገሌ ቄሮ /የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የወጣቶች ድምጽ) ሚድያ/ሬድዮ) ዜና አዘጋጆች፣ ዜና አንባቢዎች በሚል የሽብር ቡድን በማደራጀት፣ ህዝቡን ወደ አመጽና ረብሻ ውስጥ ገብቶ የሽብር ወንጀል እንዲፈፀምና መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆነ፣ እንዲሁም የግለሰቦች ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ዜና



Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

በማዘጋጀት፣ የተዘጋጀ ዜና ሪከርድ በማድረግ ውጭ ላሉት ለኦ.ነ.ግ አመራሮች እና አባሎች በመላክ በእነርሱ አማካኝነት ለተለያዩ ማህበራዊ ድረገጽ እንዲሰራጩ በማድረግ ህዝቡ ወደ አመጽ ውስጥ እንዲገባ ሲያነሳሱ የቆዩ በመሆናቸው በፈጸሙት የሽብር ድርጅት ውስጥ መሳተፍ ወንጀል ተከሰዋል፡፡

አባተ ታደሰ
የፌደራል ዐ/ህግ

ታደሰ በረደድ
የፌደራል ዐ/ህግ

**የማስረጃ ዝርዝር**

**ሊ.የሰነድ**

1. 1ኛ ተከሳሽ አሊያድ በቀለ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ/27/2 መሰረት ለፖሊስ የሰጠ የተከሳሽነት ቃል 16 ገጽ
2. 2ኛ ተከሳሽ ሞይቡል ምስጋኑ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ/27/2 መሰረት ለፖሊስ የሰጠ የተከሳሽነት ቃል 17 ገጽ
3. 3ኛ ተከሳሽ ቀነኒ ታምሩ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ/27/2 መሰረት ለፖሊስ የሰጠ የተከሳሽነት ቃል 18 ገጽ
4. 4ኛ ተከሳሽ ኢፋ ገመቹ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት ለፖሊስ የሰጠው የተከሳሽነት ቃል 14 ገጽ
5. 5ኛ ተከሳሽ ባይሉ ነጮ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት ለፖሊስ የሰጠው የተከሳሽነት ቃል 11 ገጽ
6. 6ኛ ተከሳሽ ሴና ሰለሞን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት ለፖሊስ የሰጠው የተከሳሽነት ቃል 12 ገጽ
7. 7ኛ ተከሳሽ ኤሊያስ ክፍሉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/27/2/ መሰረት ለፖሊስ የሰጠው የተከሳሽነት ቃል 06 ገጽ


ፋክስ FAX 0115-51-77-75 ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1370 ስልክ Tel. 0115-51-50-99 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiop

Scanned by CamScanner

8. የ1ኛ ተከሳሽ በቁጥር 42/57/09 በቀን በ11/7/2009 ዓ/ም የተፃፈ እና በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 14/1/ መሰረት ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የተሰበሰበ የቴክኒክ ማስረጃ 56 ገጽ
9. 1ኛ ተከሳሽ በተመለከተ ከኦሮሚያ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ከኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ አ.ማ የተላኩ ደረሰኞች እስከነትርጉሙ 6 ገጽ
10. ከ1ኛ ተከሳሽ ዲና ዲግ/Diina diigi 1215@g mail com. በሚል የኢ.ሜይል አድራሻው እና በተለያዩ የሽብር ቡድኑ አባሎች የኢ.ሜይል አድራሻ በመጠቀም ከሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የኦነግ አመራሮች እና አባሎች ጋር ሲለዋወጣቸው (ሲፃፃፍ) የነበሩ አመጽ ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው ከኢ.ሜይል አድራሻው የተገኙት፡- ጥራዝ 1፣ጥራዝ 2፣ ጥራዝ 3፣ ጥራዝ 4፣ ጥራዝ 5፣ ጥራዝ 6፣ጥራዝ 7፣ጥራዝ 8፣ ጥራዝ 9፣ ጥራዝ10፣ ጥራዝ 11፣ ጥራዝ 12፣ በጠቅላላው እስከነትርጉሙ 1008 ገጽ
11. 2ኛ ተከሳሽ በተመለከተ ከኦሮሚያ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ በቁጥር ኦኢባ/ህግ 0157/09,በቀን 2/5/2009 ዓ/ም የተፃፈ ከተከሳሹ ፎቶ ጋር 9 ገጽ
12. ከ2ኛ ተከሳሽ Gadaamacca @ gmaii.com የኢ.ሜ.ይ.ል አድራሻው እና በተለያዩ የሽብር ቡድኑ የአባሎች የኢ.ሜ.ይ.ል አድራሻ በመጠቀም ከሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙት የኦነግ አመራሮች እና አባሎች ጋር ሲለዋወጣቸው (ሲፃፃፍ) የነበሩ አመጽ ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው ከኢ.ሜይል አድራሻው የተገኙት ጥራዝ 13 እስከነትርጉሙ 78 ገጽ
13. 3ኛ ተከሳሽ በቁጥር 42/62/09,በቀን 2/8/2009 ዓ/ም የተፃፈ እና በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 14/1/ መሰረት ከብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የተሰበሰበ የቴክኒክ ማስረጃ 5 ገጽ
14. ከብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በቁጥር ደመ42/83/09 በቀን 08/04/09ዓ.ም የተላከ በኢፋ ገመቹ /4ኛ ተከሳሽ/ ላይ የቀረበ 06 ገፅ የቴክኒክ ማስረጃ
15. ብርበራ ከኢፋ ገመቹ የደበቀው ላፕቶፕ ኮሚፒውተር ሲገኝ የተያዘ ኤግዚቢት ቃለ ጉባኤ 02 ገፅ



Scanned by CamScanner

16.በቁጥር ፌፎ/112/372/2203/09 በቀን 04/07/09 ዓ.ም የተፃፈ በኢፋ ገመቹ የተፃፉ መሆናቸውን የተረጋገጠበት የፎረንሲክ ማስረጃ 09 ገፅ
17.ፍርሃትም ይሸነፋል በሚል የሚጀምር ከኢፋ ገመቹ ቤት በብርበራ የተገኘ 08 ገፅ
18.ከኢፋ ገመቹ ኢሜይል ውስጥ የወጣ /የተገኙ/ የተለያዩ የፅሁፍ ልውውጦች 278 ገፅ
19.ከባይሉ ነጮ እጅ የተገኘ የቁር ድምጽ ደንቦች የሚል ጽሁፍ 02 ገፅ
20.በቁጥር 1.2/371/52202/09 በቀን 05/07/09 የተፃፈና በሃይሉ ነጮ እጅ የተፃፈ ስለመሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ የተረጋገጠ 03 ገፅ
21.ባይሉ ነጮ ከጋሪደ ጉርሙ ጋር ያደረገው የቤት ኪራይ ውል 07 ገፅ
22.ከኤሊያስ ክፍሉ ኢሜይል ውስጥ የተገኘ/የወጣ/ የተለያዩ የፅሁፍ ልውውጦች 113 ገፅ
23.ከሴና ስለሞን ኢሜይል ውስጥ የተገኘ/የወጣ/ የተለያዩ የፅሁፍ ልውውጦች 111 ገፅ
24.በቁጥር ኦህስባ/ህአስዊ/ዳቦ/0729/15 በቀን 06/07/09 የተፃፈ ለኤሊያስ ክፍሉ ከውጭ አገር ገንዘብ የተላከለት መሆኑን የሚያሳይ 04 ገፅ ኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ የላከው ማስረጃ
25.በትጥር ቢአ/ኤም.አይ.ኤስ/70/17 በቀን 18/05/09 ዓ.ም የተፃፈ ከውጭ አገር ለኤሊያስ ክፍሉ ገንዘብ የተላከለት መሆኑን የሚያሳይ 02 ገፅ የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ የላከው ማስረጃ
26.በቁጥር ዳባ/ደሂገአ/00155/2017 በቀን 17/05/09 ዓ.ም የተፃፈ ለኤሊያስ ክፍሉ ከውጭ አገር ገንዘብ የተላከለት መሆኑን የሚያሳይ 05 ገፅ ዳሽን ባንክ የላከው ማስረጃ
27.ከኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ ኤሊያስ ክፍሉ የተላከለትን ገንዘብ ሲያንቀሳቅስ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ የባንክ ቤት ደረሰኞች 02 ገፅ
28.የኤሊያስ ክፍሉ ቤት ሲበረበር የተያዘ የብርበራ ቃለ ጉባኤ 02 ገጽ
29.የኤ.መ.ቁ 212/09 እና በኤ.መ.ቁ 211/09 የተያዘ የኤግዚቢት ደረሰኝ 02 ገጽ
30.የኤ.መ.ቁ 210/09 እና የኤ.መ.ቁ 209/09 በባይሉ ነጮ፣ሴና ስለሞን፣ቀነኒ ታምሩ፣ኢፋ ገመቹ፣ሞይቡሉ ምስጋኑ እና ኦሊያድ በቀለ የተመዘገቡበት የኤግዚቢት ደረሰኞች 02 ገጽ
31.ባይሉ ነጮ እና ኦሊያድ በቀለ ከውጭ አገር ገንዘብ ተልኮላቸው የተቀበሉ መሆኑን የሚያሳይ አዋሽ ኢንተር ናሽናል ባንክ በቁጥር አኢባ.ቸሪ.እና.ኤስ.ኤም.ኦ/ባአ/ሐ/0619/09 በቀን 06/07/09 ዓ.ም የተፃፈ 05 ገፅ
32.በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ቦታዎች ተከስቶ በነበረው ሁከትና ብጥብጥ በሰው ህይወት ፣በአካልና በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳቶችን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ 55 ገጽ


Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር
Ref.No
ቀን
Date

## ሐ.ገላጭ ማስረጃ

1. 1ኛ ተከሳሽ የኦነግ ስገሌ ቄሮ (የኦነግ የወጣቶች ድምጽ) በሚባል በተቋቋመው የሽብር ቡድን ውስጥ የሚዲያ /የሬድዮ /ዜና አንባቢ፣ አዘጋጅና ኃላፊ በመሆን የተለያዩ አመጽ ቀስቃሽ ይዘት ያላቸውን ዜና በጽሁፍ በማዘጋጀት በድምጽ ሪከርድ በማድረግ ውጭ ሀገር ለሚገኙ የኦነግ አመራሮች በመላክ በእነርሱ አማካኝነት ለተለያዩ ማህበራዊ ድረ-ገጽ እንዲሰራጭና ህዝቡ እንዲደርሱ ሲያደርጉ የነበሩት ከኢ.ሜይል አድራሻው የተገኙ ወደ 3 ሲድ የተገለበጡ በኦሮምኛ ቋንቋ ሲያቀርቡት የነበረ ዜና በችሎት የሚሰማ (የሚታይ)
2. 3ኛ ተከሳሽ የኦነግ ስገሌ ቄሮ (የኦነግ የወጣቶች ድምጽ) በሚባል በተቋቋመ የሽብር ቡድኑ ውስጥ የሚዲያ/የሬድዮ) ዜና አንባቢና ቃለ መጠይቅ አቅራቢ በመሆን አመጽ ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው የተለያዩ ሙዚቃ የኦነግ ባንዲራ ለብሰውና እያውለበለቡ ህዝቡን የሚያነሳሱበት የቅስቀሳ ዘፈኖች የያዘ ከሞባይሏ X–TIGI ከሆነ ከ4 GB ሚሞሪ ከፍታ በአዲስ ሲዲ የተገለበጠ 1 ሲዲ በኦሮሞኛ ቋንቋ የተቀነባበረ በችሎት የሚታይ/ሚሰማ)
3. 7ኛ ተከሳሽ ከኤሊያስ ክፍሉ ቤት በብርበራ ከተየገኘ ኮምፒውተር ውስጥ የተገለበጠ 02 ሲዲ ማስረጃ
4. 6ኛ ተከሳሽ ሴና ሰለሞን የዘፈነችውና በዩ ቲዩብ ላይ የለቀቀችው ዘፈኖች 01 ሲዲ ማስረጃ
5. 4ኛ ተከሳሽ ከኢፋ ገመቹ ኢሜይል ውስጥ የተገለበጡ የስገሌ ቄሮ ዜናዎች 02 ሲዲዎች
6. ኤሊያስ ክፍሉ ላይ የቀረበ ገላጭ ማስረጃ 01 ገፅ
7. ሁሉም ተከሳሾች ላይ የቀረበ ስለ ወንጀል አፈፃፀም የተዘጋጀ ገላጭ ማስረጃ 04 ገጽ

## መ.ኤግዚቢት

1.በኤግዚቢት መዝገብ ቁጥር 209/09 ቀነኒ ታምሩ፣ሴና ሰለሞን፣ባይሉ ነጮ፣ኢፋ ገመቹ፣ሞይቡል ምስጋኑ፣ኦሊያድ በቀለ ሲጠቀሙበት የነበሩበት 1 የቻይና ስሪት ቲሺባ ላፕቶፕ፣1ህዋዊ ሲዲኤም ኤ፣ 3 ሳምሰንግ ሞባይሎች፣1 ሞዴሉ mf1904 የሆነ ሲዲኤም ኤ፣5 ሲም ካርዶች፣1 X-TIG ሞባይል ከ1 ሚሞሪ ካርድ ጋር በፖሊስ እጅ የሚገኙ፡፡



Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Federal Attorney General

ቁጥር ____________
Ref.No
ቀን ____________
Date

2.2ኛ ተከሳሽ የሽብር ቡድኑ የስራ ማስፈፀሚያ የሚውል ከውጭ ሀገር ከሚኖሩ የኦነግ አመራሮች እና አባሎች ከሆኑት በተለያዩ ጊዜ የተላከለትን በቁጠባ ደብተሩ ቁጥር 217961 በሆነው .2863.31 ብር እና በቁጠባ ደብተሩ 291549 በሆነ 38345.50 በጠቅላላው 41208.81 ብር በባንኩ የሚገኝ፡፡

3. ከ2ኛ ተከሳሽ ቤት የተያዙት የገንዘብ ዝርዝር የያዙ 2 የቁጠባ ደብተሮች

4. በኤግዚቢት መዝገብ ቁጥር 211/09 1 ዴል ኮምፒውተር ከኤሊያስ ክፍሉ ቤት የተገኘ

5. በኤግዚቢት መዝገብ ቁጥር 210/09 ኢፍ ገመቹ፣ሞይቡል ምስጋኑ፣ኤሊያስ በቀለ፣ሴና ስለሞን፣ባይሉ ነጮ እና ቀነኒ ታምሩ ከተከራዩበት ቤት የተገኙ አንድ ነጭ፣አንድ ቀይ እና አንድ አረንጓዴ ቲሸርቶች በቁጥር 03

6. በኤግዚቢት መዝገብ ቁጥር 212/09 ከኤሊያስ ክፍሉ የተገኙ ኮምፒውተሮች በቁጥር 02

<u>መግለጫ</u>

1ኛ ተከሳሽ 9/3/2009 ዓ/ም ጀምሮ በፌ/ፓሊስ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡
2ኛ ተከሳሽ 26/3/2009 ዓ/ም ጀምሮ በፌ/ፓሊስ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡
3ኛ ተከሳሽ 20/2/2009 ዓ/ም ጀምሮ በፌ/ፓሊስ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡
4ኛ ተከሳሽ 21/3/2009 ዓ/ም ጀምሮ በፌ/ፓሊስ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡
5ኛ ተከሳሽ 3/4/2009 ዓ/ም ጀምሮ በፌ/ፓሊስ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡
6ኛ ተከሳሽ 24/3/2009 ዓ/ም ጀምሮ በፌ/ፓሊስ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡
7ኛ ተከሳሽ 3/4/2009 ዓ/ም ጀምሮ በፌ/ፓሊስ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡



Scanned by CamScanner